
( ከቪቫ ሚኒሊክ አምስተርዳም ፣ 14/4/2017))

## የበጋው መብረቅ(ሌፍተንት ጀነራል ጃጋማ ኬሎ)

ወደር ከማይገኝላቸው ጥቂት ጀገኖቻችን አንዱ የሆኑት ጀነራል ጃጋማ ገና ከታዳጊነታቸው ጀምሮ በአባታቸው የፈረስ ስም ጃጋማ ተብለው መጠራታቸውን ያስመሰከሩ ደፋርና ብልህ እልህኛ ጀግና ነበሩ።

ጃጋማና አዋሽ ወንዝ ከአንድ አካባቢ የመነጩ ናቸው።ጃጋማ ገና በህጻንነቱ የታላቅ ወንድሞቹ አለቃ የሆነ፤በአፍላ ወጣትነቱ የሶስት ሺህ አምስት መቶ አርበኞች መሪ የሆነ፤የራሱን ጽኑ እምነት የሚከተል፤ዘመናዊ ትምህርት ያላቸውን ውቅያኖስ አቆርጠው ሄደው ዘመናዊ የውትድርና እውቀት የቀሰሙና ዘመናዊ ኑሮ የነበራቸው ሰዎች ገባሩ የሆኑለት ጀግና ነው።

ቅድመ አያቱን ጎዳና ነሞን ይተካል እየተባለ ሲተነበይለት ያደገው ጃጋማ በአፍላ ወጣትነቱ ባልታሰበበት ቦታ የዝና መሰላል ሲወጣ ጀግንነት ሲፈጽም ታየ። የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንዲሉ የጃግሻ ተግባር የወደፊቱን የሚጠቁም ምልክት እንደሆነ ታመነ።እንደ ቅድመ አያቱ ለመሆን አንድም ቀን ሳይታከት ሲያልም ኖራልና በአድዋው ጦርነት ተሸንፋው የነበሩት ጣሊያኖች ቂም ይዘው ኢትዮጵያን በመውረርና ሕዝቦቾን  ለመበቀል በዘመናዊ ጦር ተደራጅተው በአለም የተከለከለ የጋዝ መርዝ በአይሮፕላን እያርከፈከፈ ወደነ ጃጋማ መንደር ደርሶ ሽማግሌና ህጻናትን በመግደል የወገኖቹ ቤት ሲቃጠልና ሲዘረፍ ያልተከለውን ዛፍ ሲቆርጥ ያላሳደገውን ፈረስ ሲጋልብ ሲመለከትና ወገኑ በፍርሀት ሲጨነቅ አንገቱን ሲደፋ ማየት አንጀቱን ስላሳረረው፤ወገኑን ነጻ ለማውጣት (እረ ጥራኝ ጫካው እረ ጥራኝ ዱሩ)ብሎ።በ15 አመቱ እንደተርብ ወራሬውን ለመንደፍ ተቆጥቶ  በመነሳት የቤተሰቡ የመጨረሻ ልጅ የሆነው ጃጋማ ታላላቅ ወንድሞቹን በእሱ አመራር ሰር በማድረግ በግንጪ ደን ውስጥ ሀይሉን በማሰባሰብ ለጦርነት ተዘጋጀ።በልጅነቱ ፈረስ ጉግስ አደን መሮጥና ተራራ መውጣቱ ለሰውነቱ ጥንካሬና አካባቢውን በደንብ እንዲያውቅ አድርጎታል።ጃጋማን ይበልጥ የተማመነው ግን በአባቱ እጅ የበላውና የጠጣውን የሜታን ህዝብ ነው።እንደተማመነውም የጅባትና ሜጫ ህዝብ በሙሉ ከጎኑ በመሰለፉ።በአጭር ግዜ በስሩ ብዙ ጉብሎችን በማሰከተል በወራሪ የጠላት ጦር ላይ ተደጋጋሚ ድንገተኛ ጥቃት በማድረስ በአጭር ግዜ፤ ጃጋ ጃግሻ  የብዙ ሽህ ወጣት አርበኛ መሪ ለመሆን የበቃ። ታላቅ የወገን ኩራት ሲሆን፤ለጠላት ያልጠበቁት ተርብ ሆነ።ምንንም አይነት የጦር ትምህርት የሌለው ጃግሻ በአድዋ ጦርነት ላይ የተሰለፉትን ዘመዶቹን በተለይም ቅድመ አያቱ ጎዳና ነሞን ገድል በድንብ ሲያዳምጥ ማደጉ ስለ ጦርንት ትንሽ እውቀት እንዲኖረው ረድቶታል።በመሆኑም ገና ወደ ሽፍትነት እንደገባ ከአጎቱ ልጅ ጋር በጫካ ውስጥ ሲጓዙ የጠላት አይሮፕላን በሰማይ ሲያንዣብብ የአጎቱ ልጅ አሰፋ የለበሰው ልብስ ነጭ መሆኑን አይቶ ቅጠል ሊቀባው ሲዘጋጅ አይሮፕላኑ በመቃረቡ ጃጋማ አሰፋን በስሩ አድርጎ ዶሮ ጫጭቶቻን ከአሞራ እንደምትከላከለው ከአይሮፕላን እይታ ሸፍኖ አሳለፈው፤ይህ የሚያሳየው በርቀት ከሰማይ ላይ ነጭ ልብስ መታየቱን ማወቁ ምን ያህል ጠንቃቃ እንደሆነ ነው።ይህ ብቻ አይደለም ከወፍ ቋንቋ አጥንቶ የሚስጥር የግንኙነት ቋንቋ መፍጠሩ፤እረኛጅም ዛፍ ላይ ማማ አሰርቶ በርቀት የጠላት ሰፈርንና እንቅስቃሴ የአይሮፕላን መቃራብ መመልከት መቻሉ፤በተለይም በደፈጣና በድንገተኛ የማጥቃት ስልት ብዙ ጉዳት በጠላት ላይ ማድረሱና በትንሽ የሰው ሀይል አሸናፊ መሆኑ በዘመናዊ ጦር ትምህርት ቤት ገብተው ከፍተኛ ልምድ ያላቸው የጣሊያን ጀነራሎችን ጃጋማ ጦር ትምህርት ቤት ገብቶ የተማረ ልምድ ያለው መኮንን ነው እስከማለት የደረሱበት፤ ታላቅ የጦር መሪ ሊሆን የቻለ ጀግና ነበር።

ጃጋማ በውጊያ ብቻ አልነበረም ብስለቱ በአስተዳደርም የተደነቀ ነበር።ለምሳሌ፤ከአምቦ መንገድ በላይ ያሉት ነዋሪዎች ጥራጥሬ እያዋጡ ቆሎ እየቆሉ ለአርበኛው ይረዳሉ፤ከአምቦ መንገድ በታች ያሉት ግን የጃገማ አርበኞች ሙጀሌ የወረሳቸው ሰለሆኑ ይህን የተሰነጣጠቀ እግራቸው ችሎ መራመድ አይችሉም፤ስለዚህ እንኳን እኛን ከኢጣሊያ ስራዊት ሊጠብቁን እና ሊከላከልሉን ቀርቶ ለራሳቸውም ሰለማይሆኑ በምንም ነገር አንረዳቸውም ማለታቸውን ጃጋማ ሰማ።ለሰራዊቱም ትእዛዝ ሰጥቶ ወደ ሃያ ሺህ ከብቶቻቸውን አስነዳባቸው፤ህዝቡም በጣም ተደናግጦ ምነው ምላሳችንን በቆረጠው በሚል በጣም ተደናገጡ።ቀንበራቸውን ተሸክመው የጃጋማ ጦር የሰፈረበት ቦታ ድረስ በመሄድ እግዚኦ አሉ።

ወጣቱ መሪ ጃጋማ እንዲህ አላቸው (**እኛ ከእናንተ የወጣን የእናንተ ልጆች ነን፤ጠላት የሚንቀን አንሶ ለሐገራችንና ለእናንተ በባዶ እግራችን ጠላትን ስለተዋጋን እንዴት ሙጀሊያም ትሉናላችሁ**) እኛ የወገኖቻችንን ንብረት የምንዝርፍ ተራ ውንበዴዋች አይደለንም ሁለተኛ እንዲህ እንዳታደርጉ ብሎ መክሮና አስጠንቅቆ፤ከብቶቻቸው አንድም ሳይጎድል እንዲመለስላቸው አዘዘ።

ጣሊያን ከሚያደርገው ሕዝብን የመከፋፈል አላማው አንዱ ኦሮምኛ ተናጋሪውን በአማርኛ ተናጋሪ ላይ ማነሳሳት ነው።ይሀንን ጠንቅቆ የተረዳው ጃግሻ ካአድርገው ውስጥ ለመጥቀስ ያህል፤ዘውዴ ጥላሁን የተባለ ጀግና ማይጨው የክብር ዘበኛ አባል ሆኖ ከንጉስነገስቱ ጋር የዘመተ ከደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ ጋር ሆኖ በጀልዱ ታላቅ ጀብዱ በተደጋጋሚ በመፈጸሙ።ጣልያንን መውጫ መግቢያ በማሳጣቱ የትናደዱት የጣሊያን ጦር አዛዦች በአይሮፕላን ወረቀት በመበትን ዘውዴ ጥላሁንን ያስጠጋ ወይም ቀለብ የሰጠ አካባቢው በአይሮፕላን እንደሚደበደብ ማስታወቁና በደጃዝማች ከበደ ጦር ላይ ተደጋጋሚ የአየር ጥቃት በማድረሱ ደጃዝማች ገረሱ ለግዜው ወደ ሌላ ቦታ እንዲሄድ ስለጠየቁት፤አርበኛ ዘውዴ አስራ ሁለት ተከታዮቹን ይዞ ቀኛዝማች ወዳጆ ዘንድ ሄዶ ወደ አማራ ክልል አሳልፊኝ ብሎ እንዲረዱት ተጠግቶ ሰፈረ፤ቅኛዝማች ዘውዴም ነገ ዛሬ እያሉ በጎን ጀግና ወዳጅን ጃጋማን ቶሎ እንዲመጣ አስደረጉት።ዘውዴ ጃጋማን ሲያይ ትንሽ ተከፋ፤ምክንያቱም የጃጋማ የአጎቱ ልጅ አባ ዶዮ ለጠላት አድሮል መባሉን በመስማቱ ጃጋማ አስልፎ እንዳይሰጠው ሰለፈራ ነበር።

ጃጋማ የዘውዴን ጀግንነትና ጥርጣሬ **<u>በመረዳቱ(አንተን አሳልፌ ብሰጥህ ነፍሴ አይማር፤እኔ ሳልሞት አንተ አትሞትም)</u>** ብሎ ዘውዴን ሰንጎታ ይዞት ሂዶ ስሙን አስቀይሮ ገብረማርያም አስኝቶ እስከመጨረሻው የነጻነት ቀን ድረስ በፍቅር አብረው እየዘመቱ ኖረዋል።ይህ የሚያሳየው የጃጋማን ፍጹም ኢትዮጵያዊነት ነው።

ሌላው የጃጋማ ድንቅ ስራ በሴቶች ላይ ያለው አመለካከት ነው።ጃጋማ ታላላቅ ወንድሞቹን በስሩ እንዳሰለፈው ሁሉ በትዳር ላይ የነበረችው እህቱ ሌንሴ የወንድሞቿን መሸፈት ሰምታ ትዳራን ጥላ ከነ ጃጋማ ጋር ስተቀላቀል ጃጋማ ሴት ነሽ ተመለሽ አላለም፤ እንዲያውም የስራ ድርሻ ቁስለኞችን የመንከባከብ ሃላፊነት ሰጣት።ሌላው የጃጋማ ትልቅ ችሎታ ሴቶችን በከተማ በውስጥ አርበኝነት መልምሎ የጠላትን እንቅስቃሴ ማወቅ መቻሉ ነው።ከነዚህም አንዶ ታውቂዋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ከሚሰጡት መረጃ እነጃጋማ ኢጣሊያንን ገለብው እንዲገርፉትና በተለይም የአዲስ አለም ምሽግን ለመሰበር  በጣም እረድቶቸዋል።አርበኛ ሸዋረገድ ከድል በሆላም ንጉሱንና ጃጋማን በማቅራርብ ትልቅ ሚና የተጫወቱ ታልቅ ኢትዮጵያዊት ናቸው።

ምናልባትም በኢትዮጵያ ታሪክ ጃጋማ የመጀመሪያ ኢትዮጵያ ነው፤ የማረከውን የኢጣሊያን መኮንን በገንዘብ በመሸጥ ከራሱ ከጣሊያን ጥይት እና መሳሪያ ገዝቶበት መልሶ እራሳቸውን በመረፍረፍ ጠላትን ያሳፈረ ወገኑን ያኮራ ጀግና ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ በድል መናገሻ ከተማቸው ከተመለሱ በኋላ በምእራብ ኢትዮጵያ በጅማና በኢሊባቡር ያለውን ጠላት ጠራርጎ ለማስወጣት ይህንን ዘመቻ በሃላፊነት ከሰጦቸው አንዱ ደጃዝማች ገራሱ ዱኪ ናቸው።ደጅዝማች ገርሱም ይህንን ዘመቻ በድል ለመወጣት የጃጋማና የዘውዴ ጥላሁን ጦር እንዲታዘዙላቸው ለግርማዊነታቸው ጥያቄ አቀረቡ።ንጉሱም ጃጋማ ማነው?ብለው ጥያቄ አቀረቡ፤በደጃዝማች ገረሱ በራስ አበበ በሌሎችም አርበኞች ሰለ ጃጋማ ጀግንነት በዝርዝር ተገለጻላቸው።ግርማዊነታቸውም በመገረም **<u>የጠበቅናችው ቀርተው ያልጠበቅናቸው ታሪክ ሰርተው ጠበቁን ብለው ተገርመው</u>** ለጃጋማ የዘመቻ ደብዳቤ እንዲጻፍለት ትእዛዝ ሰጡ። ትእዛዝ የደረሰው ጃጋማም መተው ጦሩን ሳላልጎበኙለት ተከፍቶ ነበርና የት ያውቁኝና ነው የሚያዙኝ ብሎ ትእዛዙን አልቀበልም አለ።ይህንን የሰሙት ንጉሥ ጃጋማ በሌላ ጦር ተከቦ ተይዞ እንዲቀርብላቸው ትእዛዝ ይሰጣሉ።ይህንን የሰሙት ታዋቂዋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ጃንሆይ ጋ በመቅረብ ሰለጃጋማ ጀግንነትና ወጣትነት በሠፊው ካስረዱ በሁላ የተቀየመው ሄደው ሳላላዩት አርበኞቹንም ሳላልጎበኙለት ነው በማለት በማስረዳታቸው፤ግርማዊነታቸውም መልካም በቅርብ መተን እናየዋለን ተዘጋጅቶ ይጠብቀን ብለው ለአርበኛዋ ሸዋረገድ ደብዳቤ አስይዘው ወደ ጃጋማ ሰደዷቸው።

ጃጋማም ደብዳቤው እንዳደረሰው ግንጪ መግቢያ ላይ ንጉሱ የሚቆሙብት ሠገነት አሰርቶ ወታደሮቹን አሰልፎ እያስፎከረ ተቀበላቸው።ንጉሠ ነገሥቱ ፊትም እንዲህ እያለ ፎከረ፤



ጎዳይ በልጅነቱ ዶቃ ሳይወጣ ካንገቱ
ጃጌ ጃጋማቸው እንደገጠመ የሚፈጃቸው
በናቱ ኦሮሞ በአባቱ ኦሮሞ
በጀግንነቱ ፈጃቸው ደግሞ
ሁሌ ያደንቃል ሀገር ተገርሞ።
እህቱም ባይ ናት ልሙት ላገሬ
የኢትዮጵያ ጀግኖች አይበገሬ።
አገሬን ከቶ አይደፍርም ጠላት፤
ዘርፎት አይወጣም ያገሬንም ህብት።
እስቲ ይለፍልህ የሀገሬ አሞራ፤
የጠላት ሬሳ ወድቆ ይዘራ።

ጃንሆይ እኔ ተኩስ እንጂ ፉከራ አልችልም ብሎ እጅ ነሳ፤ ጃንሆይም ምን ቀረህ ከዚህ በላይ በማለት ትከሻውን እየደባበሱ አሞገሱት።

በሥሩ ያሉትን አርበኞች ሸለመውና አበረታተው ከደጃዝማች ገረሱ ጋር አብሮ እንዲዘምት ነግረውት ከዘመቻ መልስ በቀጥታ እሳቸው ጋ እንዲመጣ አዘውት እንደልጃቸው እንደሚያዩት ገለፁለት።

የተሰጠውን ግዳጅ ከታላቅ ጀግንነት ጋር በድል ፈጽሞ የተመለሰው ጃግሻ እንደተባለው ንጉሡን ቀርቦ እጅ ነሳ ጃንሆይም በሰፊው ካነጋገሩት በኃላ እኛ ነን የምንድርህ ስራም እስክምንመድብህ አጠገባችን ትቀመጣለህ ብለው አዘዙት።

ጃጋማ ካወጣ ካወረደ በሆላ በጃንሆይ ምርጫ ትዳር መያዙን ሳልወደደው አቡነ ባስልዮስን እሱ የወደዳት ልጅ ሊያገባ እንደወሰነ ይህ ካልሆነ እራሱን እንደሚያጠፋ ለጃንሆይ እንዲነግሩለት አማላጅነት ልኮ ሰለተፈቀደለት ከንጉሱ ቤተሰብ የጋብቻ ሰንሰለት በማመለጡ በጣም ተደሰተ።

ጃጋማ በግርማዊነታቸው ትእዛዝ በሱም ፍላጎት 1933 አመተ ምህረት በሻለቃ ማእረግ በሆለታ ገነት ጦር ትምሕርት ቤት ገብቶ የአዛዥነት ኮርስ በመውሰድ የምድር ጦር ሰራዊትን በማቆቆምና በሃላፊነት በተለያይ እግረኛ ብርጌድ ውስጥ ከሰሩ በኃላ በውጭ ሃገር የከፍተኛ አዛዥነት ኮርስ ከወሰዱና የስራ ልምድ ካካበቱ በሆላ፤በብርጋዴር ጀነራል ማእረግ የብሔራዊ ጦር አዛዥ፤ቀጠሎም በሜጀር ጀነራል ማእረግ በአዲስ የተቆቆመውን 4ኛ ክፍለ ጦርን በአዛዥነት መርተዋል።በምድር ጦር ሰራዊት ውስጥ ባገለገሉባቸው የጦር ክፍሎች በአመራራቸውና በአስተዳደራቸው በሰራዊቱ በጣም የተከበሩና የተወደዱ በስፓርት ወዳድነታቸውም ብዙ ግዜ የጦር ሐይሎችን ስፓርት በሃላፊነት የመሩ ጀነራል መኮንን ነበሩ።




ጀነራል ጃጋማ በ1959አመተ ምሕረት በባሌ በነዋቆ ጉቱ መሪነት የተቀሰቀሰውን የገበሬዎች አመጽ በከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ግዜ የባሌ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ በመሆን ዘመቻውን በመምራት ዋቆ ጉቱ ከነተከታዮቹ እጁን እንዲሰጥ በማድረግና ለግርማዊነታቸውም በሞትና በእስራት መቅጣት ለችግሩ መፍትሄ እንደማይሆን በማስረዳት እንዲያውም በተወለደበትና በሸፈተበት ደሎ መና አውራጃ አስተዳዳሪ እንዲሆን በማማከር የባሌ ክፍለ ሐገር ሙሉ ለሙሉ ሰላማዊ እንድሆን ከማድረጋቸው በላይ በገናሌ ወንዝ ላይ ያሰሩት ድልድይ፤የዲንሾ ፓርክን በማጠርና በመከለል የመሰረቱ የሐገር ባለውለታ መኮንን ናቸው።



ሌፍተናት ጀነራል ጃጋማ ኬሎ ከአብዮት በኃላ በጡረታ ተገልለው ከሠራዊቱ ቢሰናበቱም፤ ወያኔ እስካፈረሰውና እስከ ሸጠው ድረስ ከደሞዛቸው 2 % እየተቀነሰ ካቋቋሙት መኮንኖች ክበብ አንድም ቀን ሳይለዩ በሚወዳቸውና በሚያከብሮቸው መኮንኖች (ጃከ) እንድተባሉ በፍቅርና በመወደድ የተከበሩና የታፈሩ፤ታላቅ የሰራዊቱ ድንቅና ብርቅ መመኪያ ጀነራል መኮንን ነበሩ!!!

**በጀግንነት ሐገራቸውን ከጠላት ጥቃት በተከላከሉብት ሐገር ምንም አይነት እንክብካቤና፤ለስማቸውም መታሰቢያና መጠሪያ ሳይኖራቸው በመጨረሻ የሕይወት ዘመናቸውም ተገቢ ህክምና ሳያገኙ ማረፋቸው ለመላው ሐገረ ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ልብ የሚሰብር ሐዘን ነው።**

አንበሳ መሳይ ገና ሲነሳ
ከፊት ከሆላ መድፍ እያስገሳ
የሰሜን ጋሻ የኡጋዴን ጦር
በየሄደበት የማይገበር።
የባሌ ሲዳሞ የጦሩ መሪ፤
ጃግሻ ነበር ፈጣን በራሪ።
የምድር፤የአየር፤የባሕር ሀይሉ፡
የብሔራዊ  ፓሊሱ ሁሉ
የድሮ አርበኛ አዛውንት ሁሉ፤
ጃግሻ ጃግሻ ሁሉም ይላሉ።
ጃጋ ጃግሻ የኢትዮጵያ ጀግና፡
አልሞትክም አንተ ሕያው ነህና፤
ታሪክህ በወርቅ ተጽፎልና ።



እኔም ቪቫ ሚኒሊክ ከልጅነት ጀምሮ የማውቃቸው በምክራቸው ያደኩ አብርያቸው ለረጅም ግዚ ያሳለፍኩ የእኚህ የአጼ ሃይለስላሴ የመጨረሻው ሌፍቴናት ጀነራል በሞት መለየት በመሰማቴ ከልብ ያዘነኩ መሆኔን እየገለጽኩ። የተከበሩትን ጀነራል በሻምላ ስላምታ እሰናበታለሁ!!! !!!



እትዮጵያ ሐገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፤

የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ።